# መተሳሰብ



18-30ኛው ሳምንት

2ኛ ክፍል

መጽሐፍ 13

# መተሳሰብ

መጽሐፍ 13 | 2ኛ ክፍል | 18-30ኛው ሳምንት



ይህ አጋዥ የንባብ መጽሐፍ ከዩ.ኤስ.ኤ.አይ.ዲ. (USAID) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በፓክት ኢትዮጵያ (Pact Ethiopia) እና በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ የጋራ ትብብር ተዘጋጅቶ በሴቭ ዘ ቺልድረን (Save the Children) እና በትምህርት ሚኒስቴር ተሻሽሎ ታተመ::

The CC By license lets others distribute, adjust, and build upon this work, for free or commercially, as long as credit is given to the original creation. However, any changes from the original must be indicated.
For more info please refer: *https://creativecommons.org/licenses/*



ዘላለምና ጓደኛው በአንድ የግል ትምህርትቤት ይማራሉ።



ቤታቸው ከትምህርትቤታቸው ትንሽ ይርቃል:: ሁሉም ተማሪዎች ምሳቸውን የሚበሉት በትምህርትቤታቸው ውስጥ ነው:: ከቤታቸው ያመጡትን ምሳ ሁልጊዜ ጧት ጧት ለመምህራቸው ያስረክባሉ::

መምህራቸው በየመመገቢያ
ቦታቸው ጥንቃቄ
ያስቀምጡላቸዋል፡፡

በምሳ ሰአት ሳህኖቹን ይከፍቱላቸዋል። ተማሪዎቹ የየራሳቸውን ምግብ ይመገባሉ። ዘላለምና ጓደኛው ዘወትር ጎንለጎን ተቀምጠው ይመገባሉ። አንድ ቀን እንደተለመደው እጃቸውን ታጥበው በመመገቢያ ቦታቸው ተቀመጡ።



የዘላለም ጓደኛ ስለራበው የምግቡን ሳህን ተቻኩሎ ለመክፈት ሞከረ። በድንገት የምግቡ ሳህን ከእጁ አመለጠው። ምግቡ በጠረጴዛው ላይ ተደፋ።

መምህራቸው የሌሎቹን
ተማሪዎች የምግብ ሳህን
በመክፈት ላይ ነበሩ።

የኳኳታ ድምፅ ሲሰሙ ወደነዘላለም ተመለከቱ:: የዘላለም ጓደኛ ደንግጦ ሲርበተበት አዩት:: ጠጋ ብለው የተደፋውን ምግብ ጠራርገው አነሱት:: በቆሻሻ ማጠራቀሚያ ውስጥ ደፉት:: ለወደፊቱ እንደዚህ ዓይነት ስህተት እንዳይፈጽም መከሩት::



የዘላለም ጓደኛም ሁለተኛ
እንዲህ ዓይነት ስህተት
እንደማይፈፅም ቃል በመግባት
መምህሯን ይቅርታ ጠየቀ::

ዘላለምም “ለዛሬ የእኔን ምግብ ተካፍለን እንድንበላ ይፍቀዱልን” አለ።



መምህሯም “ምግብህን ማካፈልህ ጥሩ ነው። ለአንድ ያሉት ለሁለት ይበቃል” በማለት አመስግነው ፈቀዱለት።

USAID

ከአሜሪካን ህዝብ